ከ ጎቦ ዉቃዉ ጥቅምት 11-2000
ካልጋሪ ካናዳ

# ዴ ዝ ዴ ራ ታ

“የቀስተ-ደመና ስጦታ”

እንደ ሰማይ ክዋክብት
ነፃነት በራቀበት
ግፍ በበዛባት በዚች ዓለም
የምን መፋተግ! መፋለም
የፅጌ ዲስኩር፤የ”ነጋ”ህልም
“የቀስተ-ደመና” ስጦታ. . .
የዴዚዴራታው ቅመም።

ግንማ!
ደም-እንባ የተረጨው
የወገን ሲቃ-ሰቆቃው፤
የእናት፤ የወላጅ፤ ዋይታ
በኩር ልጅዋ ሲመታ፤
በአጋዚ ጥይት እሩምታ
ሙሽራ ልጅዋ ሲመታ፤
ያነባቺው እንባ. . .
. . .በአስከሬኑ ላይ ተኝታ
የዘጠና-ሰባቱ ትዝታ
ዓሜን ብሎ መቀበል ነው. . .
. . .”የነጋ-ፅጌ” ዴዝዴራታ!።
አዲስ-ህመም፤አዲስ-በሽታ
ዓይን ያወጣ ዱለታ
የትግል-ስልት-መሸታ
ወንዝ የማያሻግር ድንፋታ
የአድር ባይነት በገና
ሆኖ ተገኝቶአልና
የፖለቲካው “ስልጠና”።

ወገኔ!

በምድር-ባገሩ ተወግዞ. . .
. . .ሲወረወር ሸዋ-ሮቢት
መቶውን ባንድ “ችግሬ”. . .
. . .ሲልጡ፤ ሲመላልጡት
. . .በተስቦም ሲጨርሱት
ያንን ግፍ ሁሉ መዓት
ራቀና እረሱት?
ምን የሚሉት ቦለቲካ?. . .
አዲስ ልክፍት! አዲስ ግኝት!
ፀሃይ የሞቀው ክህደት
መቻቻል ብሎ ቅጥፈት
መቻቻል ብሎ ቅብጠት።

ያንን የህዝብ ቁጣ. . .
. . .የግንቦቱን ማእበል
“የነጋ-በየነ” ጦስ. . .
የህዝብን ትግል ስያረክስ
ወያኔ ተሸብርኮ. . .
ሲል ግቢ-ነብስ፤ ውጪ-ነብስ
ጋሬጣ ሆናቺሁበት. . .
ዉለታዉን ይክፈሏቹ. . .
“ስብሀት-በረከት-መለስ”።

የተጋጋምው የትግል እቶን. . .
የወጣ የተመዘዘው. . .
እንደሙቀጫ ሲንከባለል
ፈንጠዚያው የማን ነው?. . .
ዴዚዴራታውን ቋጥሮ
በመለስ የመውጭያ ፍቃድ. . .
ወደ “ለንደን” የበረረው
የማን ነገረ ፈጅ ነው?

አልመሸም! አልመሸም ገና!

“ብርቱካኔ” ዴዝዴሞና
የትግል-እምቦቃቅላ
ጮርቃዋ ዴዝዴሞና
“ለነጋ-ፅጌ” ጥንጠና
“የፍልስፍና-ድህነት. . .
. . .የድህነት ፍልስፍና”
መቼ ትምጥኛና
“መዋ” እያጎ መሆኑ. . .
. . .አልተገለጠልሽም ገና?
እንደ መዥገር ተጣብቆ. . .
እግርሽ ላይ ከቶ ሽምቀቆ. . .
. . .”ነጋ” ሽንት አያስሸና
“መስፍን” አስቀምጦታል ና
የአንቺን መሂጃ ጎዳና
ከነሙሉ ክብሩ፤ስምም ሆነ ዝና፤
ቀኑ ሳይመሽ “በፅሞና”፤
“የማሪያም መንገድ ስጠኝ” በይው
ማጣፊያውን አሳጥሪው።
ሁል ግዜም የለምና፤
ሆይ ሙና! ሆይ ሙና!

አዲሱ ሶስተኛ እረድፍ
“ሊበራል” የ”ልደቱ” ግርፍ
የ”ነጋ” ፈትል. . .
. . .የ”ፅጌ” ጥልፍ
አሞት መሸጥ. . .
. . .በቁም መስነፍ
የወያኔ ዝርዝር፤ መሸሩፍ።

እኔን ስክን ያርገኝ. . .
. . .የሰከነ “ፖለቲካ”
. . .የሰከረ “ፖለቲካ”
እንዲያማ! ቢቀልማ!

እርነት በዝመማ
ወያኔስ ምን በወጣው. . .
ከእናቴ ጉሮሮ ነጥቆ. . .
አበሽ እርስ-በርሱ እንዲፋጅ. . .
. . .”አርባ-መሊዮን” የሚረጨው
. . .በንዋይ የሚጫወተው፤

የክፍለ-ዘመኑ “ኢኮኖሚስት”
እንደ “አባ-ነጋ” ትንቢት
ነፃነት!-እርነት፤ እርነት ነፃነት
ሸቀጥ አይደል. . .
. . .ከገበያ የሚገዙት
የፋብሪካ ተረፈ-ምርት
ከዛፍ የሚሸምጥጡት
እንደ ሽላ የሚለቅሙት።
ፍርድ ቤቱን፤ ፖሊሱን፤
ሬዲዮ ጋዜጣውን፤
ምርጫ ቦርድን፤ ታዛቢዉን
ቀፍድዶ የያዘው ወያኔ. . .
ታዲያስ ኢሕአፓን በምንተዳው
ያለመልኩ የምትኩለው?
እኔ ምስክር ንኝ እኔ!
ኢሕአፓ ፀረ ወያኔ!
ተነሱ! እንውጋው! የምትለው
ሕብረቱንስ በምን እዳው
አንስተህ የምትጥለው?
አገር ይስማልኝ ብልሃል
ፊስ ያለበት ዝላይ አይችል
ስጋዬ ከሩቅ ሸቶኛል
ኢሕአፓ እና ሓይሉ ያሙኛል
ዘራፍ! የመለስ አሽከር!
ሆያ ዱሬ-ኦማ ኦፌ!
ይቺ ኤቦ ኢላላ
አስወስጄ መጣሁ ለመዘፈን ችኮላ።
እኔ! አይገባኝም እኔ!
“የቀስተ-ደመና” ስልጣኔ
“”መለስን” ግን ዙር በጎኔ

እንደው በምን ስሌት በምን ቅኔ
እንዲህ ያለ ምናኔ
የሂ ነው ግፍ፤ የግፍ ግፍ. . .
ከኩነኔም ኩነኔ!

ዘመነ ግርንቢጥ!
መመራትን ሳያቅ. . .
ልምራ ብሎ መሮጥ፤
አገር ያያል በአርምሞ
ከወለጋ-ሲዳሞ
ወገን ያያል በአርምሞ
ከሃረርጌ-ደብረ-ዳሞ
“ነጋ” ፅጌን ሲሾመው. . .
. . .አበጀ! ደግ አረገ
ሃይሉ ታዬን ሲያጨው. . .
. . .ምድረ ባንዳ በረገገ
ተዬህ በላይ “ደብል-ስታንዳርድ”
ራስ መውደድ ለራስ መፍረድ
በማያሳብደው ማበድ
ትግሉን ሃዲድ አስቶ. . .
ወገንን በወሬ ፈቶ።
ዲስኩሩ ደርዝ የሌለው. . .
. . .አንዱ ካንዱ የማይግጥም
አውቆ መተኛት በቁም
ጭው-እልም፤ጭው-እልም
የቦለቲካ ልብ-ድካም
ባዶ ሕልም የቁም ሕልም
ጭው-እልም፤ጭው-እልም።

በራስ ላይ ዝመት! ክተት
የመዋ-ፅጌ ምትሃት
እንድ ግመል ሽንት የሁዋሊት
ከቃጡ ትግልን መነተት
ከእብደትም ባንዳነት!
ከባንዳነትም እብደት!

ቸር ይግጠመን